የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ
ኒውዴልሂ

**EMBASSY OF THE**
**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**
**NEW DELHI**

ቁጥር ኢኤኒ/865/288/22
**Ref. No.**

ቀን 22/06/22
**Date**

## <u>የኢትዮጵያ መንግስት በሰጠው ስኮላርሺፕ ለምትማሩ ተማሪዎች በሙሉ</u>

## <u>ህንድ</u>

የኢትዮጵያ መንግስት በሰጠው ስኮላርሽፕ በህንድ አገር በተለያዩ ዩንቨርሲቲዎች በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የሚያቀርቡትን የትምህርት ጊዜ ማራዘም /Study Time Extension/ ለትምህርት ሚኒስቴር በመላክ በሚወሰነው ውሳኔ መሰረት እየተራዘመላችሁ የነበረ መሆኑ ይታወቃል::

ይሁን እንጂ የትምህርት ሚኒስቴር ሰኔ 7 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር 04/247/691/14 በተላከልን ደብዳቤ ይህ አሰራር የአገሪቱን የፋይናንስ ሐብት ለብክነት የዳረገና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመምህራን ልማት ስራ በዕቅድ መሰረት እንዳይከናወን እያደረገ በመምጣቱ የአሰራር ለውጥ ማድረጉን አስታውቋል::

ይኸውም :-

1. የትምህርት ጊዜ ማራዘም /Study Time Extension/ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችለው ለአንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን ይህም ከአቅም በላይ መሆኑ በሃኪሞች ቦርድ ከተረጋገጠና የጤና መታወክ ሲያጋጥም ብቻ መሆኑን፣
2. የትምህርት ጊዜ ማራዘም /Study Time Extension/ ጥያቄን የትምህርት ሚኒስቴር የሚቀበለው በየጊዜው ሳይሆን በየሴሚስተሩ መጨረሻ በዓመት ሁለት ጊዜ መሆኑን ገልጿል፣

ስለሆነም የትምህርት ጊዜ ማራዘም /Study Time Extension/ ጥያቄ በተመለከተ ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተገለጸውን መመሪያ አውቃችሁ በዚሁ መሰረት ብቻ እንድትፈጽሙ እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር

**ትዝታ ሙሉጌታ (ዶ/ር)**
**ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር**


7/50 G, Satya Marg, Chanakya Puri, New Delhi -110 021
☎ : +91-11 2611 9513 / 2611 9514 Fax : +91-11 2687 5731
Email: delethem@yahoo.com, Website : www.ethiopianembassy.org.in